# በጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት ዙሪያ ያሉዎትን መብቶች ይወቁ

Seattle Public Schools

ተማሪዎች እና ሰራተኞች በማንኛውም የትምህርት ቤት ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ ውስጥ ከማንኛውም ፆታዊ ጥቃቶች እና ትንኮሳዎች ይጠበቃሉ።ይህ በት/ቤት የሚደገፍ ከካምፓስ ውጭ የሚደረግ እንቅስቃሴ፣እንደ የትምህርት ቤት አውቶቡስ ወይም የመስክ ጉዞ ያሉትን ያካትታል።

## ፆያዊ ትንኮሳ ምንድን ነው?

ፆያዊ ትንኮሳ እንደሚከተለው ይገለጻል:

- የተማሪን ትምህርት የሚያደናቅፍ ወይም ጥሩ ያልሆነ የሥራ/የትምህርት አካባቢ የሚፈጥር ያልተፈለገ ፆታዊ ስነምግባር ወይም ግንኙነት።
- ሌላ ነገር ለማግኘት ተገቢ ያልሆነ ፆታዊ ግንኙነት (እንደ ጥሩ ነጥብ፣ ወይም አዲስ የስራ መደብ ለማግኘት)።ይህ በሰራተኛ እና በተማሪ፣ወይም በሰራተኛ እና በአለቃ መካከል ሊሆን ይችላል።

ፆታዊ ትንኮሳ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል ነገር ግን በነዚህ ብቻ አይወሰንም:

- · ፆታዊ ጽሑፎችን መጻፍ
- የፍቅር ጓደኝነት ጠብ እና ማሳደድ
- ፆታዊ ቀልዶች መናገር፣ስሜት ቀስቃሽ አስተያየቶች ወይም ወሬዎች ማሰራጨት
- ፆታዊ ጽሑፎች፣ኢሜይሎች ወይም ምስሎች በመላክ
- የማይፈለጉ ፆታዊ ግስጋሴዎች

## ፆታዊ ጥቃት ምንድነው?

ፆታዊ ጥቃት በተፈጥሮ ፆታዊ የሆነ ያልተፈለገ ንክኪ ነው።ይህ ያልተፈለገ ፆታዊ ንክኪ፣ማስገደድ (አንድን ሰው ያለፈቃዱ አንድ ነገር እንዲያደርግ ማሳመን) እና አስገድዶ መድፈርን (አንድን ሰው ያለፍቃድ ወሲብ እንዲፈጽም ማስገደድ) ሊያካትት ይችላል።

አንድ ሰው ተኝቶ ወይም ራሱን ስቶ ካልሆነ በስተቀር መስማማት አይችልም።የሃይል አለመመጣጠን ካለ አንድ ሰው ላይስማማ ይችላል ለምሳሌ እንደ በሰራተኛ እና ተማሪ መካከል።

አንድ ሰው በንጥረ ነገሮች ተጽዕኖ ሥር ከሆነ ስምምነት ሊሰጥ (ሊስማማ)አይችልም።

ስለ ፆታዊ ጥቃት እና ትንኮሳ ጉዳዮች የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ፖሊሲ እና አሰራር የበለጠ መረጃ ለማግኘት ወደ ትምህርት ቤትዎ ቢሮ ይሂዱ ወይም በሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ድህረ ገጽ ላይ additional links በሚለው ስር ላይ የሚገኘውን የ Title IX ድረ-ገጽን ይጎብኙ።

## ፆታዊ ትንኮሳን ሪፖርት ማድረግ

ጾታዊ ትንኮሳ ለማንኛውም የትምህርት ቤት ሰራተኛ ወይም ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ባለስልጣናት ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ፡፡

- ለትምህርት ቤትዎ የህግ ተወካይ ባለሥልጣን: ርዕሰ መምህሩ ወይም ተወካይ
- ታይትል IX አስተባባሪ: 206-252-0367, Title.IX@seattleschools.org
- የ OSPI ፍትሃዊነት እና ሲቪል መብቶች ቢሮ: 360-725-6162, equity@k12.wa.us
- የዩኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት፣ የሲቪል መብቶች ቢሮ: 206-607-1600, OCR.Seattle@ed.gov

ሁሉም ፕሮፌሽናል የትምህርት ቤት ሰራተኞች ሪፖርት እንዲያደርጉ ይገደዳሉ።ይህ ማለት ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ፆታዊ ጥቃት ወይም ትንኮሳ ጨምሮ፣በደል ወይም ቸልተኝነት ሲደርስ ለፖሊስ ወይም ለህጻናት ጥበቃ አገልግሎት ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ጾታ፣ዘር፣ቀለም፣እምነት፣ሃይማኖት፣ብሔር፣ዕድሜ፣አካል ጉዳት፣የጋብቻ ሁኔታ፣ጾታዊ ዝንባሌ፣ጾታዊ ማንነት እና መግለጫ፣የጡረተኛ ወይም ውትድርና ሁኔታ ወይም የአካል ጉዳተኛ ሰው የአገልግሎት እንስሳ መጠቀም በመመስረት አድልዎ መፈፀም አይችልም እንዲሁም ለሁሉም የተመደቡ የወጣት ቡድኖች እኩል መዳረሻ መስጠት አለበት።ለጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች፣ እባክዎን የትምህርት ቤቱን ርእሰ መምህር፣ወይም የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶችን የተማሪ ሲቪል መብቶች ቢሮ በ 206-252-0306 ወይም በ OSCR@seattleschools.org ያነጋግሩ።

Rev. 1/2024